## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## «ነገ እንደ ዛሬው ወደ አንተ እመጣለሁና ተዘጋጅ»

በጨለማው ውስጥ አልጋዬ ላይ እንደተ ቀመጥኩኝ ለመተንፈስ እታገላለሁ ልቤ ደረቴን ሰንጥቃ ልትወጣ ትታገላለች።አየር ወደ ውስጥ በሳብኩኝ ቁጥር ብርቱ ውጋት ያሰቃየኛል።አካላቴ ሁሉ በላብ ተዘፍቋል። ሰውነቴእጅናእግሬን ማዘዝ እስኪሳነኝ ድረስ በፍርሃት ይንዘፈዘፋል። ዕንባዬ ከንፈሬን አልፎ እየገባ ምላሴን ጨውጨው ሲለኝ ይሰማኛል።

ያየሁትን ሕልም ይሁን ራዕይ መርሳትም መካድም አልቻልኩም። ከምሽቱ ሰባት ሰዓት አልፎ ወደ ቤቴ ስገባ ዛሬ ያሳለፍኩትና ለነገ በቀጠሮ ያሳደርኩት የፌሽታ ምሽት ሰውነቴን በደስታ ያቅበጠበጠው ነበር። እንደገባሁ እንደነገሩ ጸለይኩ።አባታችን የሰጡኝ ራስን መቆጣጠርያ ፎርም ሳይምልክት ሳደርግ ለመፈለግ አቅም አልነበረኝም። ነገ ይደርሳል በማለት የለበስኩትን ልብስ ከፊሉን ብቻ አውልቄ ወደ አልጋዬ ገባሁ።

ያመሸሁበት ቦታ የነበረው ምግብና መጠጥ ጨዋታው ሳቅና ሁካታው ሁሉ ልዩ ነበር።ዋው! ሕይወት እንዴት ያስደስታል።ኑሮ ማለት ይሔ ነው። ነገደግሞ የታቀደው የተለየነው።በነገው ቀጠሮና ዛሬ በነበረኝ ምሽት የደስታ ባህር ውስጥ ሰጥሜ ፈገግ አንዳንዴም ሳቅሳቅ እያለኝ እንቅልፍ ወደ እቅፉ አስገባኝ።

ምንያህል ደቂቃ ወይም ሰዓት እንደተኛሁ አላውቅም ብቻ ቀስበቀስ ነፍስ ካወኩበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ የሕይወት ጉዞዬ በፊልም እንደሚታይ እየተተረተረ ይታየኝ ጀመር።በግልጽም ሆነ በድብቅ የሠራኋቸው መልካም ነገሮችና ነውሮች ሊታዩኝ ሲጀምሩ በአየር ላይየቆምኩ ያህል ተሰማኝ።

ቀናስል ከፊትለፊቴ የሚያስደንቅ ሰማያዊ ብርሃን ታየኝ። ካለሁበት ሳልንቀሳቀስ ውስጧን ከዳር እስከዳር ላያት የቻልኩት ሀገር ተገለጠችልኝ።ምድሪቱ አረንጓዴ ምንጣፍ የተነጠፈባት ይመስል ለምለም ናት።ኅብራቸው ልብን በተመስጦ የሚሰርቅ አበቦች ፈንጠቅ ፈንጠቅ ብለው ይታያሉ።በቁመታቸው እና በግዝፈታቸው ልክ የሚያስጎመዡ ፍሬን ያዘሉ ታላላቅ ዛፎችም አሉባት።በላያቸው ላይ ከጣዕሙ የተነሳ የደረቀን አጥንት የሚያለመልም ጣዕመ ዜማን የሚያሰሙ አዕዋፋት ያዘምራሉ።ከወተት ይልቅ የሚነጣ የጠራ ታላቅ ወንዝ በውስጧ ይፈሳል። በምድሪቱ ያለ ፍጥረት ሁሉ ከታላቁ ወንዝ እየጠጣ ይረካል።በበሮቿ ላይም«የሕያዋን ምድር የታላቁ ንጉሥ ከተማ» የሚል ተጽፎባታል።በአጠገቤ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ የሆኑ በሚገርም ፍጥነት በርረው አጠገቧ ሲደርሱ ወደ ታላቅ ንስርነት ይቀየሩና በክንፋቸው የያዙትን ያወርዳሉ።ብርሃን የሚተፋ መስቀል የተቀረጸበት ነጭ ልብስ የለበሱ ና በእጃቸው የዘንባባ ዝንጣፊ የያዙ በበሮቿ ሲገቡ በዚያ ያየኋቸው አበቦች፣ታላላቅ ዛፎች፣እንዲሁም አእዋፋት ሰማዩን በታላቅ ዝማሬ ያናውጡታል።

በተመስጦ ነፍስ አልቀረልኝም።አፌን በእጆቼ ሸፍኜ በዕንባ በተሞሉ ዓይኖቼ ምድሪቱንና በውስጧ ያለውን እየተመለከትኩ ለመራመድ እግሮቼን ሳንቀሳቅስ አየር ላይ መሆኔ ታወሰኝ። ወደ እግሮቼ ስመለከት ለመቆሚያ ብቻ የምትበቃ ሰሃን የምትመስል ላይ መሆኔን አወቅሁ።አንዲት እርምጃ ተራምጄ ቢሆን ማረፊያዬን እንኳ መገመት ይቸግረኝ ነበር።

የሚያስፈራ ጨለማ ከበታቼ ተዘርግቷል።እንደ ምድጃ እሳት የሚያስፈራ ድምጽ ይሰማኛ ል። እሳቱ ብርሃናማ ባይሆንም ማየት ግን አልተሳነኝም።እቶኑ እንደ ባህር ማዕበል ያጓራል። እንደ ተራብ ሆድ ይጮሃል። የዋጠው አልበቃ ብሎት ይጎመዣል። ከመደንገጤ የተነሳ ልወድቅ ተንገዳገድኩ።ሆዴ ሲገላበጥ ሲያጥወለውለኝ ታወቀኝ። ዕንባዬም ጉሮሮዬም ደርቋል። በአጠቃላ ይበሰውነቴ ውስጥ የቀረ ፈሳሽ ያለ አልመሰለኝም። የምይዘው ነገር ፈለግሁ አላገኘሁም። ዓይኖቼን በየአቅጣጫው ላክኋቸው እነርሱም ባዷቸውን ተመለሱ። ቀናብዬ «የሕያዋን ምድር የታላቁ ንጉስ ከተማ» የተሰኘችውን ለማየት ሞከርኩ ከሥፍራዋ አልነበረችም።

በተወርዋሪ ኮከቦቹ ፈንታ አንዴ ጥላ አንዴደግሞ ጢስ የሚመስሉ ዓይናቸው ደም የጎረሰ ፍጥረታት ዙሪያዬን ይዞሩኝ ጀመር። ቅርጻቸው እንደጊንጥ፣ እንደ ሸረሪት፣ እንደ እባብ፣ እንደ ጅብ፣ ደግሞ ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው ዓይነት ቅርጽ እየያዘ ይቀያየራል። ሊተናኮሉኝ

ቀረብ ይሉና፤የሚዘገንን ስቅጥጥ የሚል ድምጽ አሰምተው ወደኋላቸው ይሸሻሉ:: የሚያሰሙት ድምጽ ነፍሴ ጥልቅ ድረስ ዘልቆ ሕመም ሲለቅባት ተሰማኝ:: ድምፁን ለማውጣት አፋቸውን ሲከፍቱ የተነፈሰ መቃብር ያህል የሚገለማ መርዛማ ሽታይ ወጣል:: ሽታው ብዙ ዓይነት ክፉ ጠረን ቢኖረውም መውጫው ግን አንድ ነበረ::

ክፉው ሽታ አካል ገዝቶ ቅርጽ ለይቶ ይታየኝ ጀመር::የማየውን ግን በፍጹም ማመን አልቻልኩም:: ያ ክፉ ሽታ የሚወጣው ከእኔው ሰውነት መሆኑን ለማመን ጊዜ ፈጀብኝ::አንዱ ሽታ ሲቀርበኝ በምድር የፈጸምኩትን የዝሙት ክርፋት እምጋለሁ፤ደግሞ የሀሰቴ ብዛት ሽታ ራሴን ያዞረዋል፤የሐሜት ጠረን ገፍትሮ ሊደፋኝ ይደርሳል፣የጥላቻዬ ፣ ሰውን የመናቄ፣ የክፋቴ፣ በሌሎች የመፍረዴ፣ ይቅርታን ያለመውደዴ፣ የአስመሳይነቴ ወዘተ. . . ብቻ ልቆጥረው ከምችለው በላይ የሆነው የኃጢአቴትን ፋገን ሁሉ አቅለሽልሾኝ ሽቅብ ይሰብቀኝ ጀመር:: በባዶው ሲፍቀኝ ነፍሴን ከማስጨነቅ በቀር ዕረፍት አልሰጠኝም:: እያንዳንዷ ድርጊቴ  ልቤን እንደስለታም ጥፍር ሲቧጥጠኝ ታወቀኝ::

በዚያች ሰሀን በምታክል ቦታ ላይ ልቅሶና ረሃብ እንዳደከመው ሕጻን እጥፍጥፍ ብዬ ተቀመጥኩኝ:: እነዚያ አስፈሪ ፍጡራን ከቀድሞው ይልቅ ቀረቡኝ:: በጥላቻ ዓይናቸው ደም ጎርሶ ሊናጠቁኝ አሰፈሰፉ:: ለአደን እንደሚያደባ ተኩላ ቀስ እያሉ እያደቡ ተጠጉኝ:: እንደ ኢዮብ የተወለድኩባትን ቀን የተጸነስኩባትንም ሌሊት ረገምኩ:: የደስታ ቀናቶቼን ፣ የመብልና የመጠጥ ምሽቶቼን፣ የእረፍት ጊዜያቶቼን፣ማስተዋል ያልጎበኘው ዘመኔን ጠላሁት:: እረፍት ያቀበጠው ሕይወቴን ቅንጦት ያሰከረው ማንነቴን ተጸየፍኩት::

ተስፋ መቁረጥ እያንዳንዷን መገጣጠሚያዬን እንደስለታም ሰይፍ እየወጋ ሲለያያቸው ተሰማኝ:: አሁን ማንንም አላይም::እሳቱንም፣ የጨለማውን አበጋዞችም፣የቀደመ ሕይወቴንም አላይም::ዓይኔ አድማስ አልቦ ውጨለማ ላይ ተሰክቷል:: ሲቃ ባነቀው ለእኔ ብቻ በሚሰማ በተረታ ድምጽ «ዋመፈጠሬ፣ ዋ ሰውመሆኔ ፣ ዋከንቱነቴ፣ዋነጻነቴ ያለፈው እንደጥላ ሸሸ የዘላለሙ ጸንቶ ቆመ የጭንቀቴ የመከራዬ የልቅሶዬ ሃሌታ ተዜመ:: ሥቃይ ልብሴ መከራም ትራሴ ለሆነ ለእኔ ወዮልኝ ወዮታ አለብኝ. . . ችላ ያልኩህ አፍቃሪዬ፣ የዘነጋሁህ እረኛዬ ፣ያላሰብኩህ ታዳጊዬ ሆይ ተመለስ! በጭንቀቴ ፈለግሁህ፤የሞት መዳፍ ከብዶኝ ሳለ ጠራሁህ፤በሰቀቀን በኃፍረቴ አማተርኩህ፤ዕረፍቴ ሆይ ተመለስ ፊትህን አትሰውርብኝ ስል ቃተትኩ:: በታላቅ ድምጽ « ኦ የዘላለም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ!. . .» ብዬ በመጮኽ ቆሜበት ከነበረው ላይቁልቁል ወደ እሳቱ ማዕበል ተውዘገዘግሁ:: እኒያ ክፉ ፍጡራን በዚያ የሚታይም ሆነ የሚሰማ በሌለበት የዝምታ ዓለም ውስጥ ሊናጠቁኝ ተወናጨፉ::

የተስፋ በር ሲዘጋ ነገም ቀድሞኝ ሲሞት ታወቀኝ:: በረዥሙ ተንፍሼ «አበቃ» በማለት ዓይኔን ጨፈንኩ::የመጨረሻዋ የእንባ ዘለላ ጉንጩን እየዳሰሰችኝ ወረደች:: የተንጣለለ መስክ ላይ ራሱን እንደሚጥል እጆቼን ወደ ጎን ዘርግቼ መጨረሻዬን እየጠበቅሁ ወደ ጥልቁ ወረድኩ::

እጆቼ ወደ ጎን በተዘረጉበት ቅጽበት እኒያ የጣዕር መናፍስት በድንጋጤ ሲታወኩና ሲጮኹ ሰማኋቸው::የሚያስፈራ ታላቅ ጸጥታ ሆነ:: ምን እየተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ፍላጎት አልነበረኝም::ሰውነቴ እሳቱ ላይ ሲያርፍ ምን ሊሰማኝ እንደሚችል በመንቀጥቀጥ ከማሰብ በቀር ምንም ነገር በኅሊናዬ አልነበረም::

ይደንቃል የምወዳቸው ቤተሰቦቼ፣የሚናፍቁኝ ባልንጀሮቼ፣ እውቀቴና ሀብቴ፣ክብሬና ውበቴ፣ መደነቄና ኩራቴ፣ዝናዬም ሆነ እብደቴ፣ ትዝታዬ መሆን አልቻሉም:: ሁሉ በፍርሃት ተውጧል:: የኃጢአት እድምተኞቼ የመዘናጋት አጋሮቼ የነበሩትን ሁሉ ለቅጽበት አሰብኳቸው::ምን እያደረጉይሆን? እኔስ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለሁያውቁ ይሆን? መጨረሻቸውን ሳስብ በዓይና፟ፊት ልጇን ሞት እንደሚነጥቃት እናት ሳግ ሆዴን አገላበጠው፤አቅመ ቢስነት አንጀቴን አቃጠለው::

ዓይኔን እንደጨፈንኩ ጠበቅሁ፤የእሳቱ ወላፈን የምድጃው ግመት ይሰማኝ ጀመር:: ልቤ ለስ እያለ በስለት እንደሚወጋ ተሰቃየች:: ወደ ላይ ለመውጣት ባለበሌለ አቅሜ ለመፍጨርጨር ሞከርኩ ግን አልቻልኩም::ከጭንቀቴ የተነሳ ምላሴን ከንፈሬን እስኪቆስል ድረስ ነከስኩት::

የብዙዎች የጣር ድምጽ የስቃይም ጩኸት ከበበኝ። ሁሉም መፈጠራቸውን በምድር የነበራቸውንም ቆይታ ይረግማሉ።ራሳቸውን ይጠላሉ።

የሲኦል ጥርስ ሲፋጭ የገሃነም ጉሮሮ ሲያዛጋ በሰማሁት ድምጽ ከመደንገጤ የተነሳ ራሴ ፈንድቶ የተበታተነ መሰለኝ። በገሃነም ሆድ ውስጥ ከመዘጋቴ በፊት በነበረች የሰኮንድ ሽፍራፊ ቅጽበት ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ፊትህን መልስ አትተወኝም! ስል ቃሌን በህዋው ላይ በተንኩት በዚያች ቅጽበት ታላቅ ነጎድጓድና ንውጽውጽታ ሆነ። ሲኦልና ሠራዊቷ ሁሉ ሸሹ ለእኔ ግን አልታወቀኝም።በፍርሃትና በድንጋጤ ጥፍር እንደተያዝኩ ዓይኔን ሳልገልጥ የሚመጣውን መጠበቅ ያዝኩ።የሚያውቀኝ ድምጽ ሲጠራኝ በኃፍረት አንገቴን እንደደፋሁ ዓይኖቼን ገለጥኳቸው። ያው ድምጽ ድጋሚ በስሜ ጠራኝ። ቀስ ብዬ ድምጹን ወደ ሰማሁበት ተመለከትኩ። ከፊትለፊቴ የቆመ ሰው በወቀሳና በሀዘን ይመለከተኛል። ፍቅሩ ያልገዛህ፣ሞቱ ያላሸነፈህ፣ቁስሉ ያልተሰማህ፣ መከራው ያልማረከህ አንተ ልብህ የማያውቀውን ቅዱስ ስሙን ስለምን በረከሱ ከንፈሮችህ በሙታን ምድር ትጠራለህ? ሲል ጽኑ በሆነ ቃል ጠየቀኝ። እመልስለት ዘንድ የተገባኝ አልነበርኩም።

ወደ ጥልቁ የሙታን መንደር በጨለማ አበጋዞች ተይዘህ ስትወርድ እጅህን ሕያው በሆነ በእርሱ መስቀል አምሳል ትዘረጋ ዘንድ ማን አስተማረህ? መስቀሉ የይቅርታ ዙፋን መሆኑን ማን አስታወሰህ? ለንስሐ በተሠጠህ ዘመን ያላሰብከውን እንዴት በሙታን ሀገር ተዘከርከው? አለኝ በተግሳጽ።

ጌታዬ ሆይ ይህ ሁሉ ከእኔ አይደለም ስለስሙ ነው እንጂ።ይቅርታ የማይገባኝ የሞት ሰው የሆንኩ እኔ አሁንም የጌታዬን ፊት አይቻለሁና ወዮልኝ! አልኩ።

አሁንም ደግሞ«ስለምን የተቀደሰ ስሙን ጠራህ፤ወደ ጥልቁስ ስትወርድ ስለምን የመስቀሉን ምልክት አደረግህ? መስቀሉ ሁልጊዜ በፊቱ እንዲታሰብ አታውቅምን?» አለኝ። እኔም መልሼ « ጌታዬ ሆይ! የጭንቀት ጣር ያዘኝ የሞት ግርማም ከበበኝ፤እደገፍበት ዘንድ ምንም ምንአጣሁ። በይቅርታው ባለጠጋ ነውና ስሙም መሐሪና ይቅር ባይ ነውና ተጣራሁ።

« አሁንም ይቅርታ ከእርሱ ዘንድ ነውና ይቅ. . .»

ቃሌን በታላቅ ቁጣ አቋረጠኝ። ይቅርታና ምህረት ለሚገባቸው ነው። አንተ በጌታ እግዚአብሔር ቸርነት ስትዘብት ቀናቶችህን ጨርሰሀቸዋል። በምድር አቆጣጠር የዛሬ ዓመት ትቆረጥ ዘንድ ከልዑሉ ዘንድ ትዕዛዝ ወጥቶ ነበር። እኔ ግን « በዚች ዓመት ደግሞ ተወው(ተዋት)» ብዬ ስላንተ አማለድኩ።የተሰጠሕን ዓመትም ለሥጋህ ብቻ በመሮጥና በከንቱ አሳለፍከው። ምንም እንኳ ስላንተ የቀረበውን ምልጃና የልዑሉንም ቸርነት እንድታውቅ ይህ በሆነበት ቅጽበት መልእክቱ አንተን እንዲጠብቅ አደራ በተሰጠው ካህን በኩል የተላከልህ ቢሆንም አልተጠቀምክበትም። የዘውትር የተለመደ ትምህርት እንጂ የተቆረጠ መልእክት አድርገህ አልወሰድከውም። ስለዚህ የተሰጠህ ጊዜ አብቅቷል።እኔም ከተጸነስክባት ቀንጀምሮ እጠብቅህ የነበርኩ ጠባቂ መልአክ ስለስሙ ክብር እና ስለመከራ መስቀሉ ይህን መልእክት እነግርህና እሰናበትህ ዘንድ መጣሁአለኝ።

የሰማሁትን ማመን አቃተኝ። አንሰራርቶ የነበረ ተስፋዬ ተሟጠጠ። ቀድሞ ያየሁት ፍርሃት ሁሉ መልሶ ነገሠብኝ። ምጥአንጀቴን ሲያኝከው ሆዴን አቅፌ ተንበርክኬ አነባሁ።

ጌታዬ ሆይ ቃልህ የታመነ ፍርድህም የተገባነው። በምድር አቆጣጠር የተረፈቺኝ ሽርፍራፊ ዲቂቃ ካለች ምህረት የተገባኝ ለመሆን እጠቀምባት ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ ስል ለመንኩት። ከአቅሙ በላይ በሆነ ግዴታ እጅግ የሚወደውን ልጁን እንደሚሰናበት ሰው ትክዝ ብሎ በዝምታ አየኝ። ወደ ላይ አሻቅቦ እያዩ በተመስጦ ከቆየ በኋላ«ነገ እንደ ዛሬው ወደ አንተ እመጣለሁና ተዘጋጅ» ብሎኝ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ወደምሥራቅ ተወነጨፈ።

ኃይሉ እንደአውሎ ነፋስ ሲወረ ውረኝ ተፈናጥሬ ከአልጋዬ ተነሳሁ። ሰዓቴን ስመለከት ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ይላል ጳጉሜን 5 ቀን 2006 ዓ.ም። ያለኝን ጊዜ አሰላሁት መፍጠን አለብኝ።እንደ እብድ ለብሼ ፊቴ በዕንባ እንደተትረከረከ ቤተክርስቲያን ንስሐአባቴን ለማግኘት

ተፈተለክሁ::ደርሼ ስጠይቅ ከአራት ቀን በፊት ቤተሰብጋር ወደገጠር እንደሔዱ ተነገረኝ:: ስልካቸውን ደጋግሜ ብሞክር ሊሠራልኝ አልቻለም:: ከውስጥ ከሚወጡ ቀሳውስት ወደ አንዱ ተጠግቼ አባቴ ላናግሮት እፈልግ ነበር አልኳቸው:: ስለምን? አሉኝ::

«አይላ ማክሮት. . . ማለቴ ንስሐ ልገባ ፈልጌ . . . ማለት በቃ ጊዜ የለኝም» እያልኩ ስቀባጥር ጤነኛ አልመሰልኳቸውም ትክብለው አዩኝ::

«ታድያ ንስሐ አባት የለህም?»

«አይ አሉኝ እከሌ ናቸው::ግን ላገኛቸው ፈልጌ ስመጣ እንደሌሉ ተነግሮኝ ነው» አልኳቸው:: የእኔ ጥድፊያ የእርሳቸውን እርጋታ አላሸነፈውም:: ታድያ በዚያው አይቀሩ ይመጣሉ:: እርሳቸው ሳያስናብቱ የሌላ ንስሐ ልጅ ኑዛዜ መቀበል አይፈቀድም:: ቢበዛ አንድ ሳምንት ቢቆዩ ነው:: አይዞህ ይመጣሉ» አሉኝ ተረጋግተው::

አንድ ሳምንት ብዬ ጮኽኩ ሳላስበው::እኔ አንድ ቀን እንኳ የሚቀረኝ ጊዜ የለኝም አልኳቸው:: አሁን ንክ መሆኔን እርግጠኛ ሆኑ መሰል ከፊል ፌዝ በጠላበት ዘይቤ« ወዴት ትሔዳለህ?» አሉኝ::

እኔ ቀኔ አልቋል ብርሃኔ ጨልሟል የመጨረሻ ቀኔ ነው እባኮትን እያልኩ ቀባጠርኩ «እኮወዴት ልትሔድ? አሉኝ ደግመው

አዲሱ ዓመት ሳይገባ እ. . . ብዬ ሳልጨርስ ተውኩት:: ቀጥሎ የሚወጣው ቃል የእብደቴ ማረጋገጫ እንደሚሆናቸው አልተጠራጠርኩም::በቆሙበት ትቼያቸው የወይራውን ዛፍ ተደግፌ ማልቀስ ጀመርኩ:: ከሳቸው በኋላ ሁለት ሦስት ቀሳውስት በአጠገቤ አለፉ::ስቅስቅ ብዬ እያለቀስኩ« ከኃጢአቴ እሥራት ይፍቱኝ» ብላቸውም በመስቀሉ ግንባሬን ገጨት ዳሰስ እያደረጉና ያላጣራሁትን ቃል እያጉተመተሙ አለፉኝ::

ለረጅም ሰዓት ቤተክርስቲያን የማደርገው ጨንቆኝ ተቀመጥኩ::ጓደኞቼ ቤተሰቦቼ ብዙ ሰው ደወለልኝ የማንንም ጥሪ መልስ አልሠጠሁም::ታላቅ ጥሪ ከፊቴ ተደቅኗል እስከዛሬ የእርሱን ጥሪ የአንድ ተራ ወዳጄን የስልክ ጥሪ ያክል እንኳ ትኩረት አልሰጠሁትም፤ዛሬ ግን ሌላ ነው::

በመጨረሻ ተነስቼ በጌታዬ የስቅለት ስዕል ሥር ተንበርክኬ ኃጢአቴን ሁሉ ተናዘዝኩ:: ከዚህ በኋላ ተስፋ የማደርገው ቸርነቱን ብቻ መሆኑን በልቤ ፍጹም አምኜ ወደ ቤቴ ጉዞ ጀመርኩ:: በመንገዴ የያዝኩትን ሁሉ ለነዳያን ከሲያል ጥርስ ከገሃነም ጉሮሮ ሥር ነጥቆ እድል ስለሰጠኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚባለው ስሙ ክብር መፀወትኩ::

ኃይለኛ ዝናብ ሲጥል ሰው ሁሉ ለመጠለል ሲራወጥ ምድር የዕንባዬ ምስክር እንድትሆን በዝናቡ እንባዬን አቀበልኳት::እንደኃጢአታችን ቢሆንከዚህ ሁሉ ዝናብ አንዲቷ ጠብታ አትሠጠንም ነበር:: እንደ ቅዱሳኑ ጸሎትና እንደቸርነቱ ግን ምድራችንን ያረሰርሳል:: ይህን እያሰብኩ ስራመድ ከፊትለፊቴ ዝናቡን ማምለጥ ያልቻለ ሁለት እግሩ ልምሾ የሆነ አንድ ሰው መሬት ለመሬት እንደቀንድአውጣ ሲሳብ አየሁት ከወገቡ በላይ ራቁቱን ነበር:: አጠገቡ ስደርስ ቀናብሎ አየኝ:: አንድ መጠለያ ሥር አቅፌ ላደርሰው ፈልጌ ባማትር ምንም ማግኘት አልቻልኩም:: ሀሳቤ ገብቶት ፈገግ ብሎ ተመለከተኝ::

ወንድሜ ሆይ ዝናቡ በጣም ደብድቦሀል ገና የሚያባራም ዓይነት አይደለም ምን ይሻላል? አልኩት::

እርሱ ደስተኛ እንደሆነ« ወዳጄ ሆይ በጥፋታቸው እየተደሰቱ በበረከታቸው ከሚማረሩት ወገን አይደለሁምና አትጨነቅ!» አለኝ:: ያልጠበኩት መልስ ነበርና አልገባኝም ግን ተደነቅሁ::

ቀስብዬ የለበስኩትን ጃኬት ከዚያም ሸሚዜን አውልቄ በየተራ አለበስኩት:: ደስ ብሎት አንድም አዲስና ዋጋቸውም ውድ ስለነበረ ከብዶት በመገረም አየኝ:: ዕረፍታችን ስለሆነው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስስትል ተቀበለኝ አልኩት::

በፈገግታ እያየኝ«ወዳጄ ሆይ ይቅር ባይ ስለሆነው ስሙ ተቀብዬሀለው» ፤ብሎ ልኩ መሆናቸውን ለማየት እጆቹን ወደ ጎንዘረጋ፤ሳያጥፋቸውም«በአዲስ ዓመት መልካም አዲስ ሕይወት» አለኝ፡፡ አሜን! ብዬ በማላውቀው ኃይል ግፊት እቅፍ አደረግሁት፡፡

ተለይቼው አንድ አሥር እርምጃ እንደተራመድኩ የእጅ ስልኬ ሲጮኸ ተሰማኝ፡፡ ጃኬቴ ኪስ እንደተውኩት አስታውሼ ዘወር ስል ሽሚዝና ጃኬቴ ተቀምጦ አየሁት ሰውየው ግን በአካባቢው የለም፡፡ ተመልሼ ማንሳት ሁሉ ፈራሁ፡፡ ቆሜ ዙሪያዬን ሁሉ ባማትር የሰው ምልክት አይታይም፡፡ በቀስታ አንስቼ ስለብሰው እንግዳ የሆነ ስሜት ተሰማኝ፡፡ ሰውነቴ ሽክም እንዳራገፈ ሲቀለኝ ቀና ብዬ ወደ ሰማዩ ተመለከትኩ፡፡ ዝናቡ ቆመ ዳመናውም ገለጠ እነሆ ፀሐይ ወጣ፡፡ከዚህ በፊት ፀሐይ አይቼ የማላውቅ ያህል ለረዥም ቆይታ በብርሃኑ ተመሰጥኩ፡፡

እቤቴ ስደርስ ለወዳጆቼና ለቤተሰቦቼ አጭር መልእክት አዘጋጀሁ፤ ምክር እንጂ ስንብት አልነበረም፡፡ ለንስሐ አባቴ የሆነውን ሁሉ መጻፍ ስጀምር በመንገድ ያገኘሁት ሰው ንግግርና ድምጽ እንደገና በጆሮዬ ማስተጋባት ጀመረ ድምፁ አዲስ ድምፅ አይደለም፤የለመድኩት ድምፅ ነው፡፡ አዎየ. .

ሰዓቱ በቀረበ ቁጥር ሰውነቴ መንቀጥቀጥ ጀመረ፡፡ ወይጉድ ማንንም አስታውሼ መደወልና መሰናበት አላሰብኩም፡፡የሞት ፍርሃት በወለደችኝ ላይ እንኳን አስጨከነኝ፡፡ ጭብጥ ብዬ በጉልበቴ ተንበረከኩ ብዙ ከማንባቴ የተነሳ እያንዳንዷ የዕንባ ጠብታ ከዓይኔ ስትወጣ እንደ እሳት ትፈጀኝ ጀመር፡፡

ኦ የዘላላም አምላክ ሆይ! የይቅርታህን ቃል መስማት የሚገባው ጆሮ በምህረትህም ሀሴት ሊያደርግ የተገባው ልቡና እንደሌለኝ አውቃለው፡፡በመጨረሻዋ ሰዓት በተግሳፅህ የተጨነቅሁት መጨነቅ ያነባሁት ዕንባ በፊትህ ትታሰብ፡፡ ወደአንተ ስመጣ የሞት ክርፋት ከኔ ይራቅ የሕይወት ማአዛ ያውደኝ፡፡ የሲኦል ምኞት አይፈጸም፤ገሀነምም ረሐብተኛ ይሁን፡፡የክፋት መናፍስት ኃይል ይሰበር፤ አለቃቸውን ቁጭት ይክበበው፤ ጨለማ ሐዘንተኛ ትሁን፡፡ ብርሃንህ በላዬ ይሁን ሠራዊትህም ያጅቡኝ፡፡ ይቅር ባይ ስምህ መጎናጸፊያዬ መስቀልህም አክሊሌ ይሁን፡፡በሕያዋን ሀገር ነፍሴ ከታላቁ ምንጭ ትርካ፤ከቅዱሳንህ ጋር ስለክብርህ ልዘምር፡፡አቤቱ ዕረፍቴ ሆይ ተመለስ ፊትህን አትሰውርብኝ! ስል ከጥልቅ ጠራሁት፡፡

የመጨረሻ ቀኔ ብትሆንም የአባቴን ቃል ለማክበር መጽሐፍ ቅዱሴን ለማንበብ አነሳሁ፡፡ከንብረቴ ሁሉ ምን ያህል ክብር የተነፈገው እንደ ነበረ አስታወስኩ፡፡ እጄ እንደመራኝ ስገልጥ «ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችንን ዛሬ ወደ እኛቀርቧልና ፡፡ ሌሊቱ አልፏል ቀኑም ቀርቧል፡፡ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ፤ በቀን እንደምንሆን በአግባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ፡፡» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር ዕንባ ባጋቱ ዓይኖቼ አንብቤ ጨረስኩ፡፡ እዚያው እንደተከዝኩ«አባቴ ሆይ በአካል አጠገቤ ባይሆኑም አምናለሁና በሰራሁት ኃጢአቴ ይቅር ይበሉኝ፤ ይፍቱኝ» ብዬ አጉተመተምኩ፡፡

የማውቀው ድምጽ ሲናገረኝ ሰማሁት፡፡ የመኝታ ቤቴ ወለል ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ እጄን ወደጎን ዘረጋሁ፡፡ ሰውነቴ በላብ ሲዘፈቅ ጉሮሮዬ ምሬቅ መዋጥ ሲከብደው ሕዋሳቴ ሁሉ ሲታወኩ ይሰማኛል፡፡ ኦ የዘላለም አምላክ ሆይ! የሚለውን ቃል በጎሲናዬ እየደጋገምኩ ተጣራሁ፡፡ ዓያኖቼ ጨፈንኩ. . . ጠበቅሁም፤ ተዘጋጅቼ እደሆን ግን አላውቅም፤እርሱ ያውቃል አዎ እርሱ ሁሉን ያውቃል፡፡

***በአዲስ ዓመት መልካም አዲስ ሕይወት!***

***እንኳን ለዘመነ ሉቃስ በሰላም አደረሳችሁ***

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

***ቀሲስ ታምራትውቤ***

***፳፻፯ዓ.ም***